የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ መጋቢት ፱ ቀን ፳፻፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 30
ADDIS ABABA, 18th March, 2025

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸/፳፻፲፯
የሲቪል እና ቤተሰብ ምዝገባ አዋጅ ………………………….................ገጽ ፲፯ሺ፱፻፮

**Content**

Proclamation No. 1370/2025
Civil and Family Registration Proclamation ………..………………………....... Page17906

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸/፳፻፲፯

## የሲቪል እና ቤተሰብ ምዝገባ ስርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማቀድ፣ የተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ዜጎች ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ እና በፍትሕ አስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ አሠራር እንዲኖር ለማስቻል የሲቪል ምዝገባ እና የቤተሰብ ምዝገባ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ በመሆኑ፤

ዜጎች ወሳኝ ኩነቶችን በአግባቡና በወቅቱ እንዲያስመዘግቡ የሚያስችል ተደራሽ፣ ሁሉን አቀፍ እና አስገዳጅ የሆነ የሲቪል ምዝገባ እና የቤተሰብ ምዝገባ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የብሔራዊ ጥቅምንና ደህንነትን ለማስጠበቅ እና በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ለዜጎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ ለማድረግ የሲቪል ምዝገባ እና የቤተሰብ ምዝገባ አገልግሎት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION No. 1370/2025

## A PROCLAMATION TO REGULATE THE CIVIL AND FAMILY REGISTRATION

**WHEREAS,** establishing a system of civil and family registration plays a key role in planning political, social, and economic developments based on reliable data, in providing different social and economic services to citizens, and in making justice administration expedient and effective;

**WHEREAS,** it has become necessary to create an accessible, comprehensive, and compulsory civil registration and family registration system that allows citizens to register vital events properly and in a timely manner;

**WHEREAS**, it has become necessary to provide civil and family registration service for the protection of national security, and for providing efficient services to citizens by the public and private sectors;



https://ethiodata.et/

የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፷/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት የማያስችል በመሆኑ አዋጁን እንደገና ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፮) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሲቪል እና ቤተሰብ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር "፩ሺ፫፻፸/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "**የሲቪል ምዝገባ**" ማለት ህብረተሰቡን የሚመለከቱ ወሳኝ ኩነቶችን እና ባህሪያቸውን በቋሚነት፣ በቀጣይነት፣ በአስገዳጅነት፣ ሁሉን አቀፍነትና ሚስጢራዊነትን በጠበቀ ሁኔታ መመዝገብ ነው፤

፪/ "**ወሳኝ ኩነት**" ማለት ልደት፣ ጋብቻ፣ ፍቺ፣ ሞት ሲሆን ጉዲፈቻን፣ ልጅነትን መቀበል፣ አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅን ይጨምራል፤

፫/ "**የክብር መዝገብ**" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሲቪል ምዝገባ እና የቤተሰብ ምዝገባ አገልግሎት መረጃዎች የሚመዘገቡበት መዝገብ ነው፤

፬/ "**የክብር መዝገብ ሹም**" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሲቪል እና የቤተሰብ ምዝገባን መረጃዎችን እንዲመዘግብ የተመደበ ሰው ነው፤

**WHEREAS,** it is important to fill the gaps in the Vital Events Registration and National Identity Card Proclamation No.760/2012 (as amended);

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Sub-Article (1) and (6) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## CHAPTER ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Civil and Family Registration Proclamation No. 1370/2025"

**2. Definitions**

In this Proclamation unless the context otherwise requires፡

1/ "**Civil Registration**" means the continuous, permanent, compulsory, universal, and confidential recording of the occurrence and characteristics of vital events about the whole population;

2/ "**Vital Event**" means birth, marriage, divorce, or death, and includes adoption, acknowledgment, and judicial declaration of paternity;

3/ "**Register of civil status**" means a register wherein particulars of civil and family registration service are recorded by this Proclamation;

4/ "**Officer of civil status**" means an officer assigned to register particulars of civil and family registration service by this Proclamation;

https://ethiodata.et/

፭/ "**አስመዝጋቢ**" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሲቪል ምዝገባን ወይም የቤተሰብ ምዝገባን የማስመዝገብ ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው፤

፮/ "**መደበኛ መኖሪያ ቦታ**" ማለት በፍትሐ ብሔር ሕግ ከአንቀጽ ፩፻፹፫ እስከ አንቀፅ ፩፻፺፩ የተደነገገውን የሚያሟላ የአንድ ግለሰብ መኖሪያ ቦታ ነው፤

፯/ "**የተከሰተበት ቦታ**" ማለት ወሳኝ ኩነት የተከሰተበት ወይም የተፈፀመበት ቦታ ነው፤

፰/ "**አገልግሎት**" ማለት የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ነው፤

፱/ "**ምዝገባ ጽሕፈት ቤት**" ማለት የሲቪል እና የቤተሰብ ምዝገባ አገልግሎት ሥራ የሚከናወንበት የክልል ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ወይም መዋቅር ነው፤

፲/ "**ቤተሰብ ማለት**" በስጋ ፣ በጋብቻ ወይም በጉዲፈቻ የሚዛመዱ እና በቋሚነት በአንድ የቤተሰብ አስተዳደር ስር በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ማለት ነው፤

፲፩/ "**የቤተሰብ ምዝገባ**" ማለት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ግለሰቦችን ለማወቅ ምዝገባ የሚካሄድበት ሥርዓት ነው፤

፲፪/ "**ለአካለ መጠን መድረስ**" ማለት የአስራ ስምንት ዓመት እድሜ መሙላት ነው፤

፲፫/ "**ክልል**" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ ዓላማ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፲፬/ "**የጤና ተቋም**" ማለት ማንኛውም የጤና አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፤

5/ "**Declarant**" means a person who has the responsibility to declare particulars of civil registration and family registration by this Proclamation;

6/ "**Principal residence**" means the place where an individual resides that satisfies the provisions of Article 183 to Article 191 of the Civil Code;

7/ "**Place of Occurrence**" means the place where a vital event occurred or was implemented;

8/ "**Service**" means the Immigration and Citizenship Service;

9/ "**Registration office**" means an office in the lowest administrative level or structure of a Region where the civil and family registration is carried out;

10/ **"Family"** according to this proclamation refers to those related by blood, marriage or adoption, and those permanently living together in one household under the same family administration;

11/ "**Family registration**" is a registration system which is conducted to identify individuals in a family;

12/ "**Attainment of the majority**" means attainment of the age of eighteen years;

13/ "**Region**" means any state referred to in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

14/ "**Health facility**" means any facility giving health services;

https://ethiodata.et/

፲፭/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፮/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

**፫. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ የሲቪል ምዝገባና የቤተሰብ ምዝገባን በተመለከተ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ እና ኢትዮጵያ ውስጥ በሚኖር በማንኛውም የውጭ አገር ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለ ሲቪል ምዝገባ

### ክፍል አንድ

### የሲቪል ምዝገባ መዝጋቢ አካላት

**፬. መዝጋቢ አካል**

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ከፌደራል እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ራሱን የቻለ አደረጃጀት ያለው ሆኖ የሲቪል ምዝገባ እና የቤተሰብ ምዝገባን ይመዘግባል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፣ የምዝገባ መረጃዎችን ያስተዳድራል፣ በብሄራዊ ደረጃ በመረጃ ቋት አደራጅቶ ይይዛል፡፡

**፭. የክብር መዝገብ ሹም**

፩/ በዝቅተኛው የአስተዳደር መዋቅር ምዝገባ ጽሕፈት ቤት የሲቪል ምዝገባ እና የቤተሰብ ምዝገባ ወይም በጤና ተቋም የልደትና ሞት ምዝገባ ወይም ፍቺ ምዝገባን በተመለከተ በመደበኛ እና እንደ አስፈላጊነቱ በሸሪአ ፍርድ ቤት የሚያከናውን የክብር መዝገብ ሹም በአገልግሎቱ ይመደባል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የተመደበ የክብር መዝገብ ሹም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት፡-

15/ "**Person**" means any natural or juridical person;

16/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. Scope of Application**

This Proclamation shall apply on civil registration and family registration to any Ethiopian and any foreign person residing in Ethiopia.

## Chapter Two

## About Civil Registration

### Section One

### Organs for Civil Registration

**4. Registration Organ**

Immigration and Citizenship Service is an independent organization with administrative structures from the Federal to the lowest administrative level that shall record, lead, coordinate, and support the tasks of civil registration and family registration activities, and shall administer and keep registration data organized in a national database at the national level.

**5. Officers of Civil Status**

1/ The Service assigns an officer of the civil status at the lowest administrative level who performs civil registration and family registration at the civil registration office or birth and death registration at a health facility or divorce registration in first-instance courts and as may be necessary sharia courts.

2/ An officer of civil status assigned under Sub-Article (1) of this Article shall, by the provisions of this Proclamation and regulations and Directives issued hereunder:

https://ethiodata.et/

ሀ) የሲቪል እና የቤተሰብ ምዝገባ ይመዘግባል፤
ለ) መረጃዎችን ወይም ቅጂዎችን ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፤
ሐ) የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለሚመለከተው ሰው ይሰጣል፤
መ) መረጃዎችን በአግባቡ አደራጅቶ ይይዛል፣ ሚስጥራዊነታቸውንም ይጠብቃል፤
ሠ) ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤
ረ) የሲቪል ምዝገባና የቤተሰብ ምዝገባ በተመለከተ ለኅብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ያከናውናል፤
ሰ) በአገልግሎቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተጨማሪ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

፫/ በኢትዮጵያ ሚሲዮን፣ በስደተኞችና ተመላሽ አገልግሎት፣ በመከላከያ ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ መርከብ ካፕቴን እንደ ክብር መዝገብ ሹም እንዲያገለግል የተመደበ ሰው ለክብር መዝገብ ሹም የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶችን ይተገብራል፡፡

a) Registers civil and family registrations;
b) Transfers data or copies to the relevant organs;
c) Issues a certificate of civil registration to the concerned person;
d) Appropriately organizes and retains data and secures their confidentiality;
e) Prepares report and transfers to the relevant organ;
f) Undertakes public awareness creation activities on civil registration and family registration;
g) Carry out other functions assigned to him by the Service.

3/ In Ethiopian missions, Refugees and Returnees Service, the National Defence Ministry, and in Ethiopian Ships Captain the person assigned to serve as officer of civil status shall carry out the tasks and responsibilities given to the officer of civil status.

## ፮. ስለ ኢትዮጵያ ሚሲዮኖች

፩/ የኢትዮጵያ ሚሲዮን በውጭ ሀገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንደ ሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤ አገልግሎቱ የክብር መዝገብ ሹም ሆኖ የሚሰራ ሰራተኛ ይመድባል፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ሚሲዮን በሌለበት ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሲቪል ምዝገባን በሚመለከት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 6. About Ethiopian Missions

1/ The Ethiopian missions shall serve as civil registration offices for Ethiopians living abroad; the Service shall assign officer of civil status.

2/ Civil Registration of Ethiopians residing in a country where there is no Ethiopian Embassy or consulate shall be carried out by Directive to be issued by the Immigration and Citizenship Service in consultation with the Ministry of Foreign Affairs.

https://ethiodata.et/

**፯. በኢትዮጵያ መርከብ ላይ ስለሚከሰት ወሳኝ ኩነት**

በኢትዮጵያ መርከብ ላይ ለሚከሰት ልደት ወይም ሞት መርከቡ እንደ ሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤ የመርከቡ ካፕቴን ከመርከቡ ሰራተኞች መካከል በየጉዞው የክብር መዝገብ ሹም ሆኖ የሚያገለግል ሰው ይመድባል፡፡

**፰. ስለ ስደተኞች**

የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ስደተኞችን በሚመለከት እንደ ሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤ እንደ ክብር መዝገብ ሹም ሆኖ የሚሰራ ሰራተኛም ይመድባል፡፡

**፱. በግዳጅ ላይ ያሉ የመከላከያ ሠራዊት አባላት**

የመከላከያ ሚኒስቴር በግዳጅ ላይ ባለ የመከላከያ ሠራዊት አባል ላይ የሚደርስ ሞት ምዝገባን በተመለከተ እንደ ሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤ እንደ ክብር መዝገብ ሹም ሆኖ የሚሠራ ሰራተኛም ይመድባል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለክብር መዝገብ

**፲. የክብር መዝገብ ዓይነቶች**

እያንዳንዱ የክብር መዝገብ የራሱ የሆነ መለያ ኮድ የሚኖረው ሲሆን የወሳኝ ኩነት ዓይነትና የምዝገባ ቦታውን የሚያመለክት ሆኖ መዘጋጀት አለበት፡፡

**፲፩ የክብር መዝገብ አዘገጃጀት**

፩/ ማንኛውም የክብር መዝገብ በጥራዝ፣ በነጠላ ወረቀት ወይም አግባብ ባለው ቴክኖሎጂ በመታገዝ በአገልግሎቱ ይዘጋጃል፤ ይደራጃል፡፡

፪/ የክብር መዝገብ በቋሚነት ለማገልገል በሚያስችልና ለአያያዝ በሚያመች ሁኔታ ይዘጋጃል፡፡

**7. Vital Events on Board Ethiopian Ships**

An Ethiopian ship shall serve as a civil registration office for the registration of birth or death that occurs on board, and the captain of the ship shall assign a staff that serves as an officer of civil status on each voyage.

**8. About Refugees**

Refugees and Returnees Service will serve as a civil registration office regarding refugees and shall assign a staff that serves as an officer of civil status.

**9. Members of Defence Forces on Active Duty**

The Ministry of Defence shall serve as a civil registration office for the registration of the death of members of the defence forces on active duty; it shall assign an officer that shall serve as an officer of civil status.

## SECTION TWO
## REGISTER OF CIVIL STATUS

**10. Types of Register of Civil Status**

Each register of civil status shall have its distinct code and shall be prepared in a way that shows the distinct type of vital event to be registered and its place of registration.

**11. Preparation of Register of Civil Status**

1/ Any register of civil status shall be prepared and organized by the Service in the form of a bound book, a separate sheet of paper, or with the support of an appropriate technology.

2/ A register of civil status shall be prepared in a durable way and manageable manner for handling.

https://ethiodata.et/

፫/ በክብር መዝገብ የሚሰፍሩ መረጃዎች በሚመለከተው ክልል የሥራ ቋንቋ እና በፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ የሚዘጋጅ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ እንግሊዘኛ ቋንቋን የሚጨምር ይሆናል፡፡

**፲፪. <u>ስለክብር መዝገብ ቅጅዎች</u>**

፩/ ማንኛውም የክብር መዝገብ በጥራዝ መልክ የተዘጋጀ ከሆነ አንድ ቀሪና ከዚሁ ቀሪ ጋር አንድ ዓይነት የሆነ መረጃዎችን የያዘ አንድ ቅጅ ይኖረዋል፡፡

፪/ የክብር መዝገብ ቅጅው ለሚመለከታቸው አካላት መላክ አለበት፡፡

፫/ የሲቪል ምዝገባው በቴክኖሎጂ የተከናወነ ከሆነ መረጃው ወዲያዉኑ ወደ አገልግሎቱ መረጃ ቋት መተላለፍ አለበት፡፡

፬/ እያንዳንዱ የክብር መዝገብ ከነቅጅው ለአንድ የወሳኝ ኩነት አይነት ምዝገባ ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

፭/ በክብር መዝገብ ላይ የተመዘገበው ወሳኝ ኩነት የአመዘጋገብ ቅደም ተከተል የሚያመለክት ማውጫ ተዘጋጅቶ መያያዝ አለበት፡፡

**፲፫. <u>የክብር መዝገብ ዝግጅትና ሥርጭት</u>**

፩/ ለክልል የሚያገለግል የክብር መዝገብ በአገልግሎቱ እና በሚመለከተው የክልል አካል ትብብር ተዘጋጅቶ በክልሉ ለሚገኙ ለሁሉም የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ይሰራጫል፡፡

3/ The information recorded on the register of civil status shall be written in the working language of the concerned Regional state and the Federal Government working language, and shall include the English language as necessary.

**12. <u>Copies of the Register of Civil Status</u>**

1/ Each civil registration form shall be accompanied by one detachable copy bearing identical particulars attached to a bound book.

2/ The detachable copy shall be sent to the concerned organs.

3/ If the civil registration is done through technology, the data shall be immediately transferred to the Service server.

4/ Each form, together with its copy, shall serve only for the registration of one vital event.

5/ An index page showing the list of events registered according to their sequence shall be prepared and attached to the register of civil status.

**13. <u>The Preparation and Distribution of Registers of Civil Status</u>**

1/ The Service shall prepare all necessary civil registration documents and forms in collaboration with the concerned Regional bodies and distribute them to all Regions and civil registration offices.

https://ethiodata.et/

፪/ ለኢትዮጵያ ሚሲዮኖች፣ ለኢትዮጵያ ባህርና ሎጀስቲክ አገልግሎት ድርጅት፣ ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር እና ለስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት የሚያገለግል የክብር መዝገብ በአገልግሎቱ ተዘጋጅቶ ይሰራጫል፡፡

፫/ የሲቪል ምዝገባው በቴክኖሎጂ የሚከወን ከሆነ አገልግሎቱ ያዘጋጀውን ቴክኖሎጂ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ለተመለከቱት አካላት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደራሽ ማድረግ አለበት፡፡

፲፬. **<u>የክብር መዝገብ ከቦታ ቦታ ስለሚንቀሳቀስበት ሁኔታ</u>**

፩/ ለስራው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ሲፈቀድ የክብር መዝገብን ከተቀመጠበት የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ወደ ሌላ ቦታ በማንቀሳቀስ የሲቪል ምዝገባውን ማከናወን ይቻላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ከቦታ ቦታ የተንቀሳቀሰ የክብር መዝገብ የሲቪል ምዝገባ እንደተጠናቀቀ ወደ ነበረበት ሲቪል ምዝገባ ጽህፈት ቤት መመለስ አለበት፡፡

፲፭. **<u>ስለ ክብር መዝገብ ደህንነት አጠባበቅ</u>**

፩/ የክብር መዝገቦችን የመያዝ ኃላፊነት ያለበት ሰው ለክብር መዝገቦቹ ደህንነት አጠባበቅ ኃላፊ ይሆናል፡፡

2/ Registers of civil status to be used by the Ethiopian missions, the Ethiopian Shipping and Logistics Services Enterprise, the Ministry of Defence, and Refugees and Returnees Service shall be prepared and distributed by the Service.

3/ If the civil registration is done through technology, the relevant technology developed by the Service shall be made accessible to the entities mentioned in Sub-Articles (1) and (2) of this article.

14. **<u>Conditions for the Moving of Registers of Civil Status from Place to Place</u>**

1/ When it is found necessary for the work and when permission is granted by the immediate supervisor the register of civil status can be moved from the civil registration office to another place to carry out civil registration tasks.

2/ The register of civil status moved from place to place by Sub-Article (1) of this article shall be returned to the civil registration office upon completion of the registration task.

15. **<u>Safeguarding Registers of Civil Status</u>**

1/ The person entrusted to keep registers of civil status shall be responsible for safeguarding the security of the registers of civil status.

https://ethiodata.et/

፪/ ለክብር መዝገቡ ደህንነትና አጠባበቅ አስጊ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ከቅርብ ኃላፊ ጋር በመመካከር በጊዜያዊነት የክብር መዝገቡን ደህንነት ለማስጠበቅ ወደሚቻልበት ቦታ አዛውሮ መያዝ ይቻላል፡፡

2/ When situations that threaten the safeguarding of the security of the Register of Civil Status occurs, in consultation with the immediate supervisor, it is possible to move the Register of Civil Status temporarily to a place where its security can be safeguarded.

**፲፮. ስለክብር መዝገብ መጥፋት፣ መውደምና መበላሸት**

፩/ የክብር መዝገብ የጠፋ፣ የወደመ ወይም የተበላሸ እንደሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ለአገልግሎቱ የተላለፉ ቅጂዎችን በመጠቀም መዝገቡን መልሶ ማደራጀት አለበት፡፡

፪/ የተቀመጠ የምዝገባ ቅጅ የጠፋ፣ የወደመ ወይም የተበላሸ እንደሆነ ለአገልግሎቱ ከተላከው የክብር መዝገብ ቅጅ በመወሰድ መተካት አለበት፡፡

**16. Loss, Destruction, and Damage of Register of Civil Status**

1/ If the register of civil status gets lost, destructed, or damaged, the office of civil status shall replace the register by using copies of the registration forms transferred to the Service in accordance with Sub-Article (2) of Article of 12 of this Proclamation.

2/ Where a copy of the registration form is lost, destructed, or damaged, it shall be replaced by the copy of the register of civil status sent to the Service.

## ክፍል ሦስት
## የሲቪል ምዝገባ ሥርዓት

## SECTION THREE
## PROCEDURES OF CIVIL REGISTRATION

### ንዑስ ክፍል አንድ
### የወል ድንጋጌዎች

### SUB-SECTION ONE
### COMMON PROVISIONS

**፲፯. መርህ**

፩/ ማንኛውም የሲቪል ምዝገባ ለሕጋዊ፣ ለአስተዳደራዊና ለስታትስቲክስ ዓላማዎች አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር መረጃዎችን በያዘ መልኩ መመዝገብ አለበት::

፪/ የሲቪል ምዝገባ በአስመዝጋቢው መደበኛ መኖሪያ ቦታ ወይም በተከሰተበት ቦታ መመዝገብ አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የሲቪል ምዝገባ ከአንድ ጊዜ በላይ መመዝገብ የለበትም፡፡

**17. Principle**

1/ Any civil registration shall be registered in a manner that contains necessary detailed information that can be used for legal, administrative, and statistical purposes.

2/ A civil registration shall be registered in the principal place of residence of the declarant or at a place of occurrence

3/ No civil registration shall be registered more than once.

https://ethiodata.et/

፬/ ማንኛውም አስመዝጋቢ የሲቪል ምዝገባን ለማስመዝገብ በክብር መዝገብ ሹም ፊት በአካል መቅረብ አለበት፡፡

፭/ የክብር መዝገብ ሹሙ የሲቪል ምዝገባ መረጃዎችን በክብር መዝገብ ቅጽ ላይ ካሰፈረ በኋላ ስለተመዘገበው መረጃ ትክክለኛነት አስመዝጋቢው እንዲያረጋግጥ ማድረግ አለበት፡፡

፮/ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር የሲቪል ምዝገባውን መዝጋቢው አካል ማከናወን ባልቻለበት ጊዜ አገልግሎቱ በሚያወጣው የምዝገባ ጊዜ ምዝገባው መከናወን አለበት፡፡

4/ A declarant shall appear in person before an officer of civil status to have a civil registration.

5/ The officer of civil status, after entering the vital event and related information in the register of civil status, shall cause the declarant to confirm the correctness of the information in the register.

6/ When the responsible organ of civil registration cannot carry out the civil registration due to force majeure, registration shall be carried out at the time announced by the Service.

## ፲፰. <u>ስለ ምዝገባ ጊዜ</u>

፩/ ሊያዘገይ የሚያስችል በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር፡-

ሀ) ማንኛውም ልደት ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ ባለው ፺ ቀናት ውስጥ፤

ለ) ማንኛውም ሞት ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ ባለው ፶ ቀናት ውስጥ፤

ሐ) ከልደት እና ሞት በስተቀር ማንኛውም ሲቪል ምዝገባ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ ባለው ፴ ቀናት ውስጥ፤

መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ የሲቪል ምዝገባ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተፈፀመ እንደሆነ አስመዝጋቢው የዘገየበትን በቂ ምክንያት በማስረጃ በማስደገፍ ማስመዝገብ አለበት፡፡

## 18. <u>Period of Registration</u>

1/ Unless and otherwise there is a sufficient reason for delay:

a/ Any birth shall be registered within 90 days of its occurrence;

b/ Any death shall be registered within 50 days of its occurrence;

c/ Any vital event other than birth and death shall be registered within 30 days of its occurrence .

2/ Where the registration of a vital event is not done within the period specified under Sub-Article (1) of this Article, the declarant shall produce sufficient reason and supporting evidence for justifying the delay.

## ፲፱. <u>የመረጃዎች አመዘጋገብ</u>

፩/ ማንኛውም የሲቪል ምዝገባ የሚመዘገበው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተዘጋጀ የክብር መዝገብ ላይ ይሆናል፡፡

## 19. <u>Entering of Particulars</u>

1/ Any civil registration shall be registered in the register of civil status prepared in accordance with Article 12 Sub-Article (1) of this Proclamation.

https://ethiodata.et/

፪/ በክብር መዝገብ የሚሰፍሩ የሲቪል ምዝገባ መረጃዎች በተዘጋጀው የመመዝገቢያ ቅጽ ክፍት ቦታ ወይም በቴክኖሎጂ በተዘጋጀው መተግበሪያ ስርዓት ላይ መመዝገብ አለባቸው፡፡

፫/ የሲቪል ምዝገባ መረጃዎችን ለመመዝገብ በጥቅም ላይ የሚውሉ ቃላት ግልፅ የሆኑና ምንም ዓይነት ምህጻረ-ቃል፣ ስርዝ፣ ድልዝ ወይም ተጨማሪ ቃል ያልተደረገባቸው መሆን አለባቸው፡፡

## ፳. ክልከላ

፩/ በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት በወጣ መመሪያ ተለይተው ከተመለከቱት መረጃዎች በስተቀር ሌላ ማንኛውንም ቃል በክብር መዝገቡ ላይ መጻፍ የተከለከለ ነው፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት በወጣ መመሪያ መሰረት ሲቪል ምዝገባ እንዲመዘገብ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳያስመዘግቡ መቆየት ክልክል ነው፡፡

፫/ የሲቪል ምዝገባንና ቤተሰብ ምዝገባን በተመለከተ ሀሰተኛ መረጃ መስጠት ወይም እውነተኛ መረጃ መደበቅ ክልክል ነው፡፡

፬/ በሀሰተኛ የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት መጠቀም ክልክል ነው፡፡

፭/ የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት አስመስሎ መስራት ወይም ወደ ሀሰት መለወጥ ክልክል ነዉ፡፡

2/ Particulars of civil registration information shall be written in the blank spaces provided in a registration form of the register of civil status or application system developed for a technology-based registration system.

3/ The particulars of civil registration information shall be written clearly and without abbreviation, erasure, overwriting, or any other additional words.

## 20. Prohibition

1/ No words other than the particulars specifically provided for in this Proclamation or Directive issued hereunder may be written on the forms of a register of civil status.

2/ Not registering a civil registration within the timeline provided by this Proclamation or appropriate Regulation is prohibited.

3/ Submitting a forged document or hiding an accurate document regarding civil and family registration information is prohibited.

4/ Using a forged civil registration certificate is prohibited.

5/ Counterfeiting or falsifying civil registration certificate is prohibited.

https://ethiodata.et/

፳፩. **ቅጾችን ስለመሰረዝ**

በጥራዝ መልክ የተዘጋጀ የክብር መዝገብ ቅጽ በስህተት ሳይሰራበት የተዘለለ እንደሆነ ወይም በስርዝ ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት አንድ ምዝገባ እንደገና መከናወን ያለበት ከሆነ ቅጹ መስቀለኛ የሆኑ ሁለት መስመሮች ተደርገውበት ይሰረዛል፤ በጀርባው ላይም "ያልተሰራበት ቅጽ" የሚል ሀረግ ይጻፍበታል፡፡

፳፪. **የተመዘገቡ መረጃዎችን ስለማረጋገጥና ስለማጽደቅ**

፩/ ማንኛውም የሲቪል ምዝገባ መረጃ አስመዝጋቢ በክብር መዝገቡ ላይ ስለሰፈሩት መረጃዎች ትክክለኛነት በፊርማው ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ የክብር መዝገብ ሹሙ የሲቪል ምዝገባ መረጃው የተሟላ መሆኑን አረጋግጦ በመፈረም ማጽደቅ አለበት፡፡

፳፫. **ስለ ፊርማ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በክብር መዝገብ የሰፈሩ መረጃዎችን በፊርማው ማረጋገጥ ያለበት ሰው:-

፩/ ፊርማውን በጽሁፍ መፈረም አለበት፤

፪/ በጽሁፍ መፈረም የማይችል ከሆነ የጣት አሻራውን በምዝገባ ቅጹ ላይ ማኖር አለበት፤

፫/ በጽሁፍ ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት የጣት አሻራውን በምዝገባ ቅጹ ላይ ማድረግ የማይችል ከሆነ መፈረም ያልቻለበት ምክንያት ተገልጾ እንዲፈርምለት የሚፈለገው ሰው ምስክር ባለበት ይፈርማል፤

፬/ የሲቪል ምዝገባው በቴክኖሎጂ የሚከናወን ከሆነ በተቀመጠው የቴክኖሎጂ ሥርዓት መሰረት መፈረም አለበት፡፡

21. **Voiding Forms**

If a form for the registration of civil status prepared in a bounded book form has been skipped or left unutilized by mistake or if, on account of erasure or for any other cause, a recording must be redone, the form shall be voided by drawing two crossing lines; and the phrase "Form not Utilized" shall be written on its backside.

22. **Confirmation and Approval of Records**

1/ Any declarant of civil registration information shall confirm, by signing, the validity of particulars written on the register of civil status.

2/ The officer of civil status shall confirm the completeness of records and approve by signing.

23. **Signature**

A person required to confirm the particulars written on a register of civil status in accordance with Article 22 Sub-Article (1) of these proclamation:

1/ shall sign in writing;

2/ if he is unable to sign in writing, he shall put his fingerprint on the registration form;

3/ if unable to sign in writing and with his fingerprints due to a disability, the reasons why he is unable to sign shall be described and a person of his choice shall sign for him in the presence of witnesses;

4/ if the civil registration is done through technology, it shall be signed through the technological system provided.

https://ethiodata.et/

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ስለ ልደት ምዝገባ

### ፳፬. የልደት ምዝገባ ይዘት

የልደት ምዝገባ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት:-

፩/ የተመዝጋቢው ሙሉ ስም፣ ፆታ፣ የተወለደበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት፣ የትውልድ ቦታ፣ የልደቱ ዓይነት (ነጠላ ወይም ከአንድ በላይ) እና በልደት ጊዜ የተደረገ እርዳታ፤

፪/ የወላጆች ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት፣ የትውልድ ቦታ፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ዜግነት፣ የአስመዝጋቢው ፊርማ፤

፫/ የልደቱ አስመዝጋቢ ከወላጆቹ አንዱ በሆነ ጊዜ በህግ አግባብ ለማስመዝገብ የሚያበቁ ማስረጃዎችን ማቅረብ አለበት፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም የተፈለገውን ማስረጃ ማቅረብ የማይችል መሆኑ ከተረጋገጠ በቀረበው ወላጅ ብቻ ተፈርሞ ይመዘገባል ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል፤

፭/ አስመዝጋቢው ወላጅ ያልሆነ እንደሆነ ሞግዚት ወይም አሳዳሪ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፣ የአስመዝጋቢው ሰው ሙሉ ስም፣ ከተመዝጋቢው ጋር ያለውን ዝምድና፣ ፆታ፣ የትውልድ ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት፣ የትውልድ ቦታ፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታና ፊርማ፤

፮/ የክብር መዝገብ ሹሙን ሙሉ ስምና ፊርማ፣ የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤቱን ማኅተምና የምዝገባውን ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት፤ እና

## SUB-SECTION TWO

## REGISTRATION OF BIRTH

### 24. Particulars of Records of Birth

The records of birth registration shall contain the following particulars:

1/ the civil registrant's full name, sex, date, month, and year of birth, place of birth, type of birth (whether single or more), and aid rendered during birth;

2/ the child's parents' full name, date (day, month, and year) of birth, place of birth, place of principal residence, marital status, citizenship, the signature of the declarant;

3/ where the declarant is one of the parents of the child, he shall present evidences that enable him to be a declarant;

4/ notwithstanding the provision in Sub-Article (3) of this article, where it is proved that the declarant parent is unable to provide the required evidence, it shall be recorded and signed only by the parent that came to declare and the details of its execution will be determined by regulations;

5/ where the declarant is other than the parent of the child, the guardian's or custodian's full name, relation with the child, sex, date (day, month, and year) of birth, place of birth, principal place of residence, and signature;

6/ name and signature of the officer of the civil status, seal of the civil registration office, and date (day, month, and year) of registration; and

https://ethiodata.et/

፯/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ አገልግሎቱ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ሊጨምር ይችላል።

**፳፭. <u>ወላጆቹ ለጊዜው ያልታወቁ ህፃን ልደት ምዝገባ</u>**

ለጊዜው ወላጆቹ የማይታወቅ ህፃን ልደት ምዝገባ፡-

፩/ ህፃኑ የተሰጠው ስም፣ ፆታ፣ ይሆነዋል ተብሎ የሚገመተውን ዕድሜ፣ የተገኘበትን ቀን፣ ወር እና ዓመት ምህረት እና ቦታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎችን፣ እና

፪/ በምዝገባ ቅጹ ጀርባ ላይ "ወላጆቹ ለጊዜው ያልታወቁ ህፃን" የሚል መግለጫ መያዝ አለበት፡፡

**፳፮. <u>ልደትን የማስመዝገብ ግዴታ</u>**

፩/ ወላጆች የህጻን ልጃቸውን ልደት በዚህ አዋጅ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው፡፡

፪/ ወላጆች የሌሉ እንደሆነ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ልደቱን የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

፫/ ለግዜው ወላጆቹ ያልታወቁ ህፃን የሆነ እንደሆነ ይህንን ሁኔታ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ወይም አግባብ ላለው ለሌላ የሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሪፖርት የደረሰው ፖሊስ ወይም ማንኛውም አግባብ ያለው ሌላ የሚመለከተው አካል በ፲ ቀን ውስጥ በአቅራቢያው በሚገኘው የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት የክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ቀርቦ ልደቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

7/ The Service may include other necessary particulars as stipulated by the Regulation issued by the Council of Ministers.

**25. <u>Particulars of Records of Birth of a Child Whose Parents are Unknown</u>**

The records of birth registration of a child whose parents are temporarily unknown shall contain:

1/ the name given to the child, sex, estimated age of the child, and the date (day, month, and year) and place in which the child was found; and

2/ a phrase "a child whose parents are unknown" on the backside of the registration form.

**26. <u>Obligation to Register Birth</u>**

1/ The parents are obliged to register the birth of a child as per the given due date in this Proclamation.

2/ If his parents are not present, the custodian or guardian of the child is obliged to register the birth of the child.

3/ Where his parents are temporarily unknown, any person knows such condition shall have the duty to report same to the nearest police or other relevant government organ.

4/ A police officer or any other government organ that has received a report in accordance with Sub-Article (3) of this Article shall have the duty to declare the birth to the officer of the civil status of the nearest civil registration office with in 10 days from the date of receipt of the report.

https://ethiodata.et/

፭/ በጎዳና ላይ የሚኖሩ ህፃናትን በተመለከተ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአቅራቢያው በሚገኘው የሲቪል ምዝገባ አስተዳደር ጽህፈት ቤት የክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ቀርቦ ልደቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

፮/ ልደቱ የተከሰተው በማረሚያ ቤት ውስጥ የሆነ እንደሆነ ማረሚያ ቤቱ የህፃኑን እናት ልደቱን በአቅራቢያ በሚገኝ የሲቪል ምዝገባ ጽህፈት ቤት እንድታስመዘግብ ማድረግ አለበት።

፯/ ልደቱ የተከሰተው በአዳሪ ትምህርት ቤት ወይም በሌላ የጋራ መኖሪያ ሥፍራ ውስጥ የሆነ እንደሆነ የተቋሙ ኃላፊ የህፃኑን እናት ልደቱን በአቅራቢያ በሚገኝ የሲቪል ምዝገባ ጽህፈት ቤት እንድታስመዘግብ ማድረግ አለበት።

## ፳፯. ስለ ስም

፩/ የክብር መዝገብ ሹሙ ልደትን ከመመዝገቡ በፊት ለልደት ተመዝጋቢው የተሰጠውን ወይም ሊሰጠው የታሰበውን ስም አስመዝጋቢውን መጠየቅ አለበት፡፡

፪/ ለልደት ተመዝጋቢው የተሰጠው ስም ለክብር መዝገብ ሹሙ ያልተነገረው እንደሆነ ወይም የተሰጠው የግል ስም ሕግን ወይም የህብረተሰቡን ባህልና ልማድ የሚቃረን ከሆነ አስመዝጋቢው የልደት ተመዝጋቢውን ስም እንዲነግረው ወይም እንዲለውጥ መጠየቅ አለበት።

## ፳፰. ስለ ልደት ምዝገባ ቦታ

፩/ የልደት ምዝገባ ቦታ በወላጆች፣ በሞግዚት፣ በአሳዳሪ መደበኛ መኖሪያ ቦታ በሚገኝ የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ወይም ልደቱ በተከሰተበት ቦታ በሚገኝ ሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ወይም የጤና ተቋም ነው፤

5/ Regarding children living on the street, the Ministry of Women and Social Affairs shall have the duty to declare the birth to the officer of the civil status of the nearest civil registration office.

6/ If the birth occurred in a prison, the institution shall make the mother of the child get the birth of her child registered.

7/ If the birth occurred in boarding school or any other communal dwelling place, the person who is in charge of such institution shall declare the birth for registration.

## 27. About the Name

1/ The officer of civil status, prior to the registration of birth, shall enquire about the name given or intended to be given by the declarant.

2/ Where the name is not disclosed or the name given is contrary to the law or the society's culture and custom, the officer of the civil status shall ask the declarant to tall him or change the name.

## 28. Place of Registration of Birth

1/ The place of registration of birth of a child shall at the civil registration office the principal place of residence of the parents, guardians, or custodians of the child or at the civil registration office or health facility where the birth occurred;

https://ethiodata.et/

፪/ ወላጆቹ ያልታወቀ ህፃን የልደት ምዝገባ ቦታ ህፃኑ በተገኘበት ቦታ አቅራቢያ በሚገኝ የሲቪል ምዝገባ ጽህፈት ቤት ነው፡፡

**፳፱. ስለጉዲፈቻ፣ ልጅነትን መቀበል እና አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅ ምዝገባ ቦታ**

የጉዲፈቻ፣ ልጅነትን መቀበል እና አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅ ምዝገባ ቦታ ስምምነቱን ባጸደቀው ወይም ውሳኔውን በሰጠው ፍርድ ቤት አቅራቢያ በሚገኝ ሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ወይም በአስመዝጋቢዎቹ መደበኛ መኖሪያ ቦታ በሚገኝ የሲቪል ምዝገባ ጽህፈት ቤት ነው፡፡

**፴. ልደትን ስለ ማሳወቅ**

፩/ ልደቱ የተከሰተው በጤና ተቋም ውስጥ እንደሆነ ተቋሙ አግባብ ያላቸውን መረጃዎች የያዘ የልደት ማሳወቂያ ወረቀት ወዲያውኑ ሞልቶ ልደቱን የማስመዝገብ ግዴታ ላለበት ሰው መስጠት አለበት፡፡

፪/ ልደቱ የተከሰተው ከጤና ተቋም ውጪ የሆነ እንደሆነ በዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ላይ ያለው የጤና መዋቅር ወይም የጤና ባለሙያ አግባብ ያላቸውን መረጃዎች የያዘ ማሳወቂያ ወረቀት ወዲያውኑ ሞልቶ ልደቱ የተከሰተበት ቦታ ለሚገኘው ሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ማሳወቅ አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የተሰጠ የልደት ማሳወቂያ ወረቀት የክብር መዝገብ ሹሙ ፊት ቀርቦ የልደት ምስክር ወረቀት ካልተሰጠው በቀር ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡

2/ The place of registration of birth of a child whose parents are unknown shall be the nearest civil registration office to the place where the child was found.

**29. Place of Registration of Adoption, Acknowledgement, and Judicial declaration of paternity**

The place of registration of adoption, and acknowledgment of a child's judicial Declaration of paternity shall be at the civil registration office nearest to the court that passed the decision or the civil registration office nearest to the principal place of residence of the declarants.

**30. Notification of Birth**

1/ Where birth takes place in a health facility, the facility shall forthwith prepare notification paper containing the relevant particulars and hand it over to the person having the duty to declare the birth.

2/ Where birth takes place outside of a health facility, the health facility structure or professional found in the lowest administrative unit shall immediately fill the appropriate particulars on a form and notify the civil registration office found at the place where the birth occurred.

3/ The notification paper of birth registration given under Sub-Article (1) of this Article shall have no legal effect unless presented to the officer of civil status and the officer of civil status issues a birth certificate.

https://ethiodata.et/

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ስለጋብቻ ምዝገባ

**፴፩. ስለ ጋብቻ ምዝገባ ይዘት**

የጋብቻ ምዝገባ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

፩/ የተጋቢዎችን ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት፣ የትውልድ ቦታ፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ፣ ዜግነት፣ የምስክሮች ሙሉ ስምና ፊርማ፤

፪/ ጋብቻው የተከናወነበት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት፣ ቦታና ሥርዓት፤

፫/ የተጋቢዎች፣ የተጋቢው ወይም የተወካይ ፊርማ፤

፬/ እንደሁኔታው ጋብቻው ስለመፈጸሙ የቀረበ ማስረጃ፤

፭/ የክብር መዝገብ ሹሙን ስምና ፊርማ፣ የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤቱን ማኅተምና የምዝገባውን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት፤ እና

፮/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ አገልግሎቱ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ሊጨምር ይችላል።

**፴፪. ጋብቻን የማስመዝገብ ግዴታ**

፩/ ጋብቻው የተፈፀመው በክብር መዝገብ ሹም ፊት ከሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ ጋብቻውን ወዲያውኑ መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ጋብቻው በኃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ሥርዓት የተፈፀመ እንደሆነ ተጋቢዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ የተመለከተውን ማስረጃ ለክብር መዝገብ ሹም በማቅረብ ጋብቻውን ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

## SUB-SECTION THREE

## REGISTRATION OF MARRIAGE

**31. Particulars of Records of Marriage**

The records of marriage shall contain the following particulars:

1/ The couples' full name, date (day, month, and year) of birth, place of birth, principal residence, citizenship, full name and signature of witnesses;

2/ The date (day, month, and year), place, and form of the marriage;

3/ The couples' or their delegates' signature;

4/ Evidence presented indicating the marriage was performed the case may be;

5/ The name and signature of the officer of civil status, the seal of the office of civil registration, the date (day, month, and year) of registration; and

6/ The Service may include other necessary particulars as stipulated by the Regulation issued by the Council of Ministers.

**32. Obligation to Declare Marriage**

1/ Where marriage is performed before an officer of civil status, the officer of civil status shall immediately register the marriage.

2/ Where marriage is performed by religious or customary ceremony, the couples shall present to an officer of civil status, for registration, the evidence of the marriage referred to in Article 34 of this Proclamation and get the marriage registered.

https://ethiodata.et/

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም በህግ አግባብ ከተፈቀደ ከሁለቱ ተጋቢዎች አንደኛው ተጋቢ ወይም ተወካይ ጋብቻው ከተፈፀመ በኃላ ሕጋዊ ውክልና ይዞ በመቅረብ ጋብቻውን ማስመዝገብ ይችላል፡፡

፬/ ጋብቻው በእንደራሴ የተፈፀመ ከሆነ ከሚመለከተው የፍትህ አካል ማስረጃ በማቀርብ ከተጋቢዎቹ አንደኛው ቀርቦ ጋብቻውን ማስመዝገብ ይችላል።

## ፴፫. የጋብቻ ምዝገባ ቦታ

የጋብቻ ምዝገባ ቦታ ጋብቻው የተፈፀመበት ቦታ፣ ከተጋቢዎቹ አንዱ ይኖርበት የነበረ መደበኛ መኖሪያ ቦታ ወይም ከተጋቢዎቹ የአንደኛው ወላጆች ወይም አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት የተደነገገውን የዝምድና ደረጃ መሰረት በቅርብ ዘመዶች መደበኛ መኖሪያ ቦታ በሚገኝ የሲቪል ምዝገባ ጽህፈት ቤት ነው፡፡

## ፴፬. በኃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ሥርዓት የተፈጸመ ጋብቻ ማስረጃ

፩/ ጋብቻው የተፈፀመው በኃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ሥርዓት መሠረት ከሆነ፡-

ሀ) የተጋቢዎቹን ሙሉ ስም፣ ዕድሜና መደበኛ መኖሪያ ቦታ፤

ለ) ጋብቻው የተፈጸመበትን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት እና ቦታ፤ እና

ሐ) የምስክሮችን ሙሉ ስም፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ እና ፊርማቸውን፤

3/ Notwithstanding the provision of this Sub Article (2) of this article, one of the spouse or a legal representative can register the marriage after the marriage has taken place, if permitted by Law.

4/ Where the marriage is performed by a delegate and where evidence is presented from the relevant justice organ, one of the couples can appear and get the marriage registered.

## 33. Place of Registration of Marriage

The place of registration of marriage shall be the civil registration office found in the place where the marriage is performed, the place where either of the couples had used to reside as their place of principal residence or the principal residence of the parents or close relative of either of the couples.

## 34. Evidence of Religious or Customary Marriage

1/ Where the marriage is performed by religious or customary practice, the religious institution or the elders who have observed the marriage shall immediately provide the couples with evidence of the marriage containing the following:

a) the full names, ages, and principal residences of the couples;

b) the date (day, month, and year) and place of the marriage; and

c) the names, principal residences, and signatures of the witnesses;

https://ethiodata.et/

የያዘ የጋብቻ ማስረጃ ጋብቻውን ባስፈፀመው የኃይማኖት ተቋም ወይም ጋብቻውን ባስፈጸሙት ሽማግሌዎች ለተጋቢዎቹ ወዲያውኑ መሰጠት አለበት፡፡

፪/ የክብር መዝገብ ሹሙ በኃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ሥርዓት የተፈፀመውን የጋብቻ ማስረጃ በመቀበል ጋብቻውን ይመዘግባል፡፡

**ንዑስ ክፍል አራት**

**ስለ ፍቺ ምዝገባ**

፴፭. **የፍቺ ምዝገባ ይዘት**

የፍቺ ምዝገባ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

፩/ የተፋቺዎችን ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት፣ የትውልድ ቦታ፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ፣ ዜግነት፣ ፍቺው የተፈፀመበት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት፣ ቦታ፤

፪/ ጋብቻው የተፈፀመበትን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት እና ቦታ፤

፫/ ስለ ፍቺው መፈፀም ሥልጣን ባለው መደበኛ ወይም የሸሪዓ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ወይም ማስረጃ፤

፬/ የክብር መዝገብ ሹሙን ስምና ፊርማ፣ የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤቱን ማህተምና የምዝገባውን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት፤ እና

2/ The officer of civil status shall take the evidence of the marriage performed by a religious and customary practice and register the marriage.

**SUB-SECTION FOUR**

**REGISTRATION OF DIVORCE**

35. **Particulars of Records of Divorce**

The records of divorce shall contain the following particulars:

1/ The full names of the divorcing partners, their date (day, month, and year) and place of birth, their principal residence, their citizenship, the date (day, month, and year) and place in which the divorce took place;

2/ The date (day, month, and year) and place of conclusion of the marriage;

3/ An evidence or decision provided by the competent Regular or Sharia Court on the completion of divorce;

4/ The name and signature of the officer of the civil status, the seal of the office of civil registration, and the date (day, month, and year) of registration; and

https://ethiodata.et/

፭/ የሚኒስትሮች ም/ቤት በሚያወጣው ደንብ አገልግሎቱ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ሊጨምር ይችላል።

**፴፮. <u>ፍቺን የማስመዝገብ ግዴታ</u>**

ተፋቺዎች በጋራ፣ ከተፋቺዎቹ አንዱ ወይም የተፋቺው ተወካይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ (፫) የተጠቀሰውን የውሳኔ ማስረጃ ለክብር መዝገብ ሹም በማቅረብ የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባለው ፴ ቀን ውስጥ ፍቺውን ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

**፴፯. <u>የፍቺ ምዝገባ ቦታ</u>**

የፍቺ ምዝገባ ቦታ ፍቺው በተፈጸመበት አቅራቢያ በሚገኝ የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ወይም በተፋቺዎች ወይም በተፋቺው መደበኛ መኖሪያ ቦታ በሚገኝ የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ነው፡፡

**፴፰. <u>የፍቺ ማስረጃ</u>**

፩/ የፍቺ ውሳኔ የሰጠ ማንኛውም ፍርድ ቤት የውሳኔውን ቅጅ ለተፋቺዎቹ ወዲያውኑ መስጠት አለበት፡፡

፪/ ማንኛዉም ተቋም ከፍቺ ማስረጃ ጋር ተያያዥነት ያለውን አገልግሎት ለመስጠት የሚችለው ተገልጋዩ የፍቺ ምስክር ወረቀት ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለ ሞት ምዝገባ</u>

**፴፱. <u>የሞት ምዝገባ ይዘት</u>**

የሞት ምዝገባ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

፩/ የሟች ሙሉ ስም፣ ማእረግ፣ ፆታ፣ እድሜ፣ ሥራ፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ፣ ዜግነት፤

5/ The Service may include other necessary particulars as stipulated by the Regulation issued by the Council of Ministers.

**36. <u>Obligation to Declare Divorce</u>**

The divorcing partners, one of them, or the delegate of the divorcing partner shall present the evidence of the decision as mentioned in Sub-Article (3) of Article 35 of this Proclamation to an officer of the civil status for registration of the divorce within 30 days from the date of the divorce decision.

**37. <u>Place of Registration of Divorce</u>**

The place of registration of divorce shall be the nearest civil registration office to the place where the divorce took place or the place of principal residence of the divorcing partners.

**38. <u>Evidence of Divorce</u>**

1/ Any court that has rendered a decision on divorce shall forthwith provide copies of the decision to the divorcing partners.

2/ Any institution can provide services associated with evidence of divorce only when the user provides it with a certificate of divorce.

## <u>SUB-SECTION FIVE</u>

## <u>REGISTRATION OF DEATH</u>

**39. <u>Particulars of Records of Death</u>**

The records of death shall contain the following particulars:

1/ The full name, title, sex, age, occupation, principal residence, and nationality of the deceased;

https://ethiodata.et/

፪/ የሞቱን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት፣ ቦታ፣ ምክንያትና ሞቱን የሚያረጋግጠውን ማስረጃ የሚያመለክት መግለጫ፤

፫/ የክብር መዝገብ ሹሙን ስምና ፊርማ፣ የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤቱን ማህተምና የምዝገባውን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት፤ እና

፬/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ አገልግሎቱ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ሊጨምር ይችላል።

## ፵. ሞትን የማስመዝገብ ግዴታ

፩/ ከሟች ጋር አብሮ ይኖር የነበረ ሰው ሟች መሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ከሟች ጋር አብሮ ይኖር የነበረ ሰው የሌለ እንደሆነ የሟች የስጋ ወይም የጋብቻ ቅርብ ዘመድ፣ እነዚህ የሌሉ እንደሆነ ስለሟቹ መሞት የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ሟች መሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሰረት የማስመዝገብ ግዴታ የተጣለበት ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሰረት ከጤና ተቋም፣ ከኃይማኖት ተቋም ወይም ከዕድር የተሰጠውን ሟች መሞቱን ማሳወቂያ ወረቀት መሰረት በማድረግ ወይም ከእነዚህ አደረጃጀቶች ማሳወቂያ ወረቀት ባልተሰጠ ጊዜ አስመዝጋቢዉ በራሱ የሚያዉቃቸውን መረጃዎች በመስጠት ሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

2/ Date (day, month, and year), place, and cause of the death, and a reference to evidence of the death, if any;

3/ The name and signature of the officer of the civil status, the seal of the civil registration office, and the date (day, month, and year) of registration; and

4/ The Service may include other necessary particulars as stipulated by the Regulation issued by the Council of Ministers.

## 40. Obligation to Declare Death

1/ Any person who used to live with the deceased shall declare the death for registration.

2/ In the absence of persons who used to live with the deceased, his relatives by consanguinity or affinity, in the absence of these, any person who knows his death shall declare the death for registration.

3/ The person who have an obligation to declare the death for registration according to Sub-Articles (1) and (2) of this Article shall according to Sub-Articles (5) of Article 42 of this Proclamation declare the death for registration based on the notification of the death given by a religious institution or Edir or declare the information he knows and get is registered when notification is not given by these structures.

https://ethiodata.et/

፬/ በአደጋ ወይም ባልታወቀ ምክንያት ሞቶ ማንነቱ ስላልታወቀ አስከሬን ሪፖርት የተቀበለ ፖሊስ ሪፖርቱ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት ፭ የስራ ቀናት ውስጥ ሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

**፵፩. <u>በግዳጅ ላይ ስላለ የመከላከያ ሠራዊት አባል ሞት</u>**

የመከላከያ ሠራዊት አባል በግዳጅ ላይ እያለ ከሞተ የክፍሉ አዛዥ በመከላከያ ሚኒስቴር እንደ ክብር መዝገብ ሹም እንዲሰራ ለተመደበው ሰው ሞቱን በማሳወቅ ማስመዝገብ አለበት፡፡

**፵፪. <u>በጋራ መኖሪያ ሥፍራ፣ በማረሚያ ቤት ወይም በጤና ተቋም ስለተከሰተ ሞት</u>**

፩/ ሞቱ የተከሰተው እንደ አዳሪ ትምህርት ቤት፣ የጋራ መኖሪያ ስፍራ ወይም በመሳሰሉት የሆነ እንደሆነ የተቋሙ ኃላፊ ወይም ተቋሙ ሞቱን እንዲያስመዝግብ የወከለው አካል በ ፭ የስራ ቀን ውስጥ ሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ሞቱ የተከሰተው በማረሚያ ቤት ውስጥ የሆነ እንደሆነ ወይም የሞት ቅጣት ፍርድ የተፈጸመ እንደሆነ ማረሚያ ቤቱ በአምስት የስራ ቀን ውስጥ ሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

4/ Any police who have received a report on the death of a person by accidental or unknown cause and whose identity is not known shall declare the death for registration with in 5 working days following the date of receiving of the report.

**41. <u>Death of Member of Defence Force on Active Duty</u>**

The death of a member of the defence force on active duty shall be declared, for registration, by the commanding officer of his unit to the officer assigned by the Ministry of Defence to act as an officer of civil status.

**42. <u>Death Occurring in Common Dwelling Place, Prison or Health Facility</u>**

1/ If a person dies in a boarding school or in any other common dwelling place, the person who oversees such institution or an organ delegated to declare the death for registration by the institution shall declare the death for registration with in 5 working days.

2/ If a person dies in prison or if a death sentence is executed, the head of the prison shall declare the death for registration within five working days.

https://ethiodata.et/

፫/ ሞቱ የተከሰተው በጤና ተቋም ውስጥ ከሆነ ወይም አስክሬን ለምርመራ ወደ ጤና ተቋሙ የመጣ እንደሆነ ተቋሙ የሟችን ስም፣ ፆታ፣ የትውልድ ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት፣ የሞተበትን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት፣ የሞተበትን ቦታና የሞት ምክንያት እና የመሳሰሉ መረጃዎችን የያዘ የሞት ማሳወቂያ ወረቀት ወዲያውኑ ሞልቶ ሞቱን የማስመዝገብ ግዴታ ላለበት ሰው መስጠት አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው የሞት ማሳወቂያ ወረቀት የክብር መዝገብ ሹሙ ፊት ቀርቦ የሞት ምስክር ወረቀት ካልተሰጠው በቀር ህጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡

፭/ ሞቱ የተከሰተው ከጤና ተቋም ውጪ የሆነ እንደሆነ በዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ላይ ያለው የጤና መዋቅር ወይም የጤና ባለሙያ አግባብ ያላቸውን መረጃዎች የያዘ ማሳወቂያ ቅጽ ወዲያውኑ ሞልቶ ሞቱ የተከሰተበት ቦታ ለሚገኘው ሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡

፮/ የቀብር ስነ-ስርዓት የተፈፀመበት የኃይማኖት ተቋም ወይም ዕድር ቀብሩን ለመፈፀም ለሚመጣው ግለሰብ ወይም ሞቱን እንዲያስመዘግብ ግዴታ ለተጣለበት ሰው የሞት ማሳወቂያ ወረቀት ይሰጣል፡፡

፯/ የበጎ አድራጎት መርጃ ድርጅቶች በድርጅታቸው ውስጥ የተከሰተ ሞትን በአቅራቢያቸው ለሚገኝ ሲቪል ምዝገባ ጽህፈት ቤት ሞቱን ማስመዘገብ አለባቸው፡፡

3/ Where a death occurs in a health facility or a corpse is brought to it for examination, the head of the facility shall forthwith prepare a notification paper of death containing the name, sex, and date (day, month, and year) of birth of the deceased, the date (day, month and year), place and cause of death and other related information and give the certificate to the person having the responsibility of declaring the death for registration.

4/ The notification of death given under Sub-Article (3) of this Article shall have no legal effect unless presented to the officer of civil status and given a death certificate.

5/ Where a death occurs outside a health facility, the health facility structure or professional in the lowest administrative structure shall forthwith fill a notification form containing relevant particulars and declare it to the civil registration office nearest to the place of occurrence of the death.

6/ The religious institution or Edir in which the burial ceremony took place shall give written notification of the death to the person having the responsibility of declaring the death for registration;

7/ Charity organizations shall declare a death occurring in their organization, for registration, to the nearest civil registration office.

https://ethiodata.et/

**፵፫. <u>በአደጋ ምክንያት ስለሞቱ ብዙ ሰዎች</u>**

በአደጋ ምክንያት ብዙ ሰዎች በአንድ ላይ በሞቱ ጊዜ አደጋው ከደረሰባቸው ሰዎች መካከል ከአደጋው በኋላ ሊገኝ ያልቻለ ሰው ስለአደጋው መከሰትና የጠፋው ሰው በአደጋው ወቅት ከሟቾቹ ጋር አብሮ የነበረ ስለመሆኑ ባጣራው አካል የተሰጠ ማስረጃ ሲቀርብ ሞቱ ይመዘገባል፡፡

**፵፬. <u>ስለ ሞት ምዝገባ ቦታ</u>**

፩/ የሞት ምዝገባ ቦታ በሟች መደበኛ መኖሪያ ቦታ ወይም ሞቱ በተከሰተበት ቦታ አቅራቢያ በሚገኝ ሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ወይም የጤና ተቋም ነው፡፡

፪/ ማንነቱ ወይም መደበኛ መኖሪያ ቦታው ለማይታወቅ ሟች የሞት ምዝገባ ቦታ አስከሬኑ በተገኘበት ቦታ አቅራቢያ በሚገኝ ሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ነው፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚፈጸም የሞት ምዝገባ ቦታ በአስመዘጋቢው ተቋም አቅራቢያ የሚገኝ የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ይሆናል፡፡

**፵፭. <u>ስለ መጥፋት</u>**

፩/ ማንኛውም በህግ አግባብ የሌላን ሰው የመጥፋት ውሳኔ ያሰጠ ሰው የውሳኔውን ግልባጭ በጠፋው ሰው የመጨረሻው መደበኛ መኖሪያ ቦታ አቅራቢያ ለሚገኘው የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት የክብር መዝገብ ሹም አቅርቦ ሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

**43. <u>Death of Several Persons by Accident</u>**

Where several persons die simultaneously due to an accident, the death of a person who disappeared thereafter shall be registered upon presentation of evidence issued by the organ that has investigated the occurrence of the accident and the presence of that person among the victims during the accident.

**44. <u>Place of Registration of Death</u>**

1/ The place of registration of death shall be the nearest civil registration office or health facility to the principal residence of the deceased or the place of occurrence of the death.

2/ Where the identity or principal residence of the deceased is unknown, the place of registration of death shall be the nearest civil registration office to the place where his corpse was found.

3/ The place of registration of death referred to under Sub-Article (1) of Article 42 of this Proclamation shall be the nearest civil registration office to the institution declaring the death.

**45. <u>Absence</u>**

1/ Any person who has, upon submitting an application to the competent court in accordance with the relevant provisions of the Civil Code, obtained a judicial declaration on the absence or death of a person shall present a copy of the judgment, for registration of death, to the officer of civil status of the nearest civil registration office to the last principal residence of the person whose absence or death has been declared.

https://ethiodata.et/

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመዘገበ ሞትን የሚመለከት የመጥፋት ውሳኔን የሚሽር ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተሰጠ ሌላ ውሳኔ ለክብር መዝገብ ሹሙ የደረሰው እንደሆነ የቀድሞው የሞት ምዝገባ መሰረዝ አለበት፡፡

2/ The records of death registered in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be cancelled where the officer of civil status receives another judgment rendered by a competent court revoking the previous judgment declaring absence.

## ክፍል አራት

## ስለ ሲቪል ምዝገባ ቅጂ እና የምስክር ወረቀት

## SECTION FOUR

## COPIES AND CERTIFICATE OF CIVIL REGISTRATION

### ፵፮. የምዝገባ ቅጂን ስለማስተላለፍ

፩/ የሲቪል ምዝገባ የተከናወነው በጥራዝ ከሆነ ምዝገባው በተከናወነ በ፵፭ ቀናት ውስጥ የክብር መዝገብ ሹሙ የምዝገባ ቅጂን አግባብ ላለው የክልሉ አካል መላክ አለበት።

፪/ የሲቪል ምዝገባው የተከናወነው በቴክኖሎጂ ከሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ ምዝገባው እንደተከናወነ ወዲያውኑ ለአገልግሎቱ መላክ አለበት፡፡

፫/ አገልግሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የደረሰውን መረጃ አግባብ ላለው የክልል አካል ተደራሽ ማድረግ አለበት፡፡

፬/ አግባብ ያለው የክልል አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የደረሰውን የምዝገባ ቅጽ ቅጂ በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ለአገልግሎቱ መላክ አለበት፡፡

### 46. Transfer of Copies of Records

1/ Where the civil registration is done in bound book, the officer of civil status shall send a copy of the registration form to the appropriate regional organ within 45 days following the date of registration.

2/ Where the civil registration is completed through technology, the officer of the civil status shall upon the completion of the civil registration forthwith send it to the Service.

3/ The Service shall send copies of the registration form it has received in accordance with Sub-Article (2) of this Article to the appropriate regional organ.

4/ The appropriate regional organ shall send copies of the registration form it has received in accordance with Sub-Article (1) of this Article to the Service within 30 days following the date of receipt.

https://ethiodata.et/

፭/ የኢትዮጵያ ሚሲዮን የሲቪል ምዝገባ ባጠናቀቀ በ፴ ቀናት ውስጥ የምዝገባ ቅጹን ቅጂ ለአገልግሎቱ መላክ አለበት፣ የሲቪል ምዝገባው በቴክኖሎጂ ከሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ ምዝገባው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ለአገልግሎቱ መላክ አለበት፡፡

፮/ የመከላከያ ሚኒስቴር እያንዳንዱን በግዳጅ ላይ ያለ የመከላከያ ሠራዊት አባል ሞት ምዝገባ ባጠናቀቀ በ፴ ቀናት ውስጥ የምዝገባ ቅጽ ቅጂ ለአገልግሎቱ መላክ አለበት፤ የሲቪል ምዝገባው በቴክኖሎጂ ከሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ ምዝገባው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ለአገልግሎቱ ማስተላለፍ አለበት፡፡

፯/ የኢትዮጵያ መርከብ ካፒቴን የሲቪል ምዝገባ በተጠናቀቀ በ፴ ቀናት ውስጥ የምዝገባ ቅጽ ቅጂ ለኢትዮጵያ ባህርና ሎጀስቲክ አገልግሎት ድርጅት መላክ አለበት፤ የኢትዮጵያ ባህርና ሎጀስቲክ አገልግሎት ድርጅት የደረሰውን የምዝገባ ቅጽ ቅጂ በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ለአገልግሎቱ መላክ አለበት፡፡ የሲቪል ምዝገባው በቴክኖሎጂ ከሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ ምዝገባው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ለአገልግሎቱ ማስተላለፍ አለበት፡፡

5/ An Ethiopian missions shall send copies of the registration form to the Service within 30 days following the date of completion of the civil registration; Where the civil registration is completed through technology, the officer of civil status shall upon the completion of the civil registration forthwith send it to the Service.

6/ The Ministry of Defence shall send copies of each of the registration forms of the death of a member of the defence force on active duty to the Service; Where the civil registration is completed through technology, the officer of civil status shall upon the completion of the civil registration forthwith send it to the Service.

7/ The captain of an Ethiopian ship shall send copies of the registration form to the Ethiopian Shipping and Logistics Services Enterprise within 30 days following the date of completion of the civil registration; the Ethiopian Shipping and Logistics Services Enterprise shall send copies of the registration within 30 days of the receipt to the Service; Where the civil registration is completed through technology, the officer of civil status shall upon the completion of the civil registration forthwith send it to the Service.

https://ethiodata.et/

፰/ የስደተኞችና ተመላሽ አገልግሎት የሲቪል ምዝገባ በተጠናቀቀ በ፴ ቀናት ውስጥ የምዝገባ ቅጽ ቅጂ ለአገልግሎቱ መላክ አለበት፤ የሲቪል ምዝገባው በቴክኖሎጂ ከሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ ምዝገባው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ለአገልግሎቱ ማስተላለፍ አለበት፡፡

፱/ ለአገልግሎቱ በዚህ አንቀጽ መሰረት የደረሰውን የምዝገባ ቅጽ ቅጂ በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ለስታቲስቲካዊ አገለግሎት የሚውሉ የተመረጡ መረጃዎችን ለኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት መላክ አለበት፤ የሲቪል ምዝገባው በቴክኖሎጂ የተከናወነ ከሆነ የተመረጡ መረጃዎችን ወዲያውኑ ለኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት መላክ አለበት።

**፵፯. <u>የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት አዘገጃጀት</u>**

፩/ አገልግሎቱ የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት ያዘጋጃል፡፡

፪/ የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት በዚህ አዋጅ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች መሠረት በክብር መዝገብ ላይ ከሰፈሩት ውስጥ ወሳኝ የሆኑና የተመረጡ መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡

፫/ ለፌደራል የሲቪል ምዝገባ መዝጋቢ አካላት የሚዘጋጀው የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት በፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ መሆን አለበት፡፡

8/ The Refugees and Returnees Service shall send copies of the registration form to the Service within 30 days of the completion of the civil registration; Where the civil registration is completed through technology, the officer of civil status shall upon the completion of the civil registration forthwith send it to the Service.

9/ The Service shall, upon receiving copies of the civil registration form in accordance with this Article, send particulars selected for statistical purposes to the Ethiopian Statistical Service within 30 days following the date of receiving. Where the civil registration is completed through technology, it shall forthwith send particulars selected for statistical purposes to the Ethiopian Statistical Service.

**47. <u>Preparation of Certificate of Civil Registration</u>**

1/ The Service prepares a civil registration certificate.

2/ A certificate of civil registration shall contain the essential and selected particulars registered in the register of civil status pursuant to the relevant provisions of this Proclamation.

3/ Certificate for the Federal civil registration organs shall be prepared in the federal government working language and in English.

https://ethiodata.et/

፬/ ለክልል ሲቪል ምዝገባ ጽህፈት ቤት የሚዘጋጀው የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት በክልል የሥራ ቋንቋና በፌደራል መንግስት የሥራ ቋንቋ እንደ አስፈላጊነቱ፡ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ይሆናል፡፡

**፵፰. <u>የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>**

፩/ የልደት ምዝገባ ምስክር ወረቀት በዚህ አዋጅ መሠረት ልደቱን ላስመዘገበው ሰው ይሰጣል፡፡

፪/ ልጅነት የመቀበልና አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅ ምዝገባ ምስክር ወረቀት በዚህ አዋጅ መሠረት ልጅነት የመቀበልና አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅን ላስመዘገበ ሰው የልደት ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፫/ የጋብቻ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በሁለት ቅጂዎች ተዘጋጅቶ ለእያንዳንዱ ተጋቢ ይሰጣል፡፡

፬/ የፍቺ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በሁለት ቅጂዎች ተዘጋጅቶ ለእያንዳንዱ ተፋቺ ይሰጣል፡፡

፭/ የሞት ምዝገባ ምስክር ወረቀት በዚህ አዋጅ መሠረት ባለመብት ለሆነ ሰው ይሰጣል፡፡

፮/ የጉዲፈቻ ምዝገባ ምስክር ወረቀት በዚህ አዋጅ መሠረት ጉዲፈቻውን ላስመዘገበው ሰው ይሰጣል፡፡

4/ Certificate for the Regions civil registration organs shall be prepared in the official language of the Region and Federal working language; if necessary, in English.

**48. <u>Issuing Certificate of Civil Registration</u>**

1/ A certificate of registration of birth shall be given to the person who has declared the birth in accordance with this Proclamation.

2/ A certificate of birth for the acknowledgment of a child and judicial declaration of paternity shall be given to the person who has acknowledged the child and who is declared a father by the court of law in accordance with this proclamation.

3/ A certificate of registration of marriage shall be prepared in two copies and be given to each spouse.

4/ A certificate of registration of divorce shall be prepared in two copies and be given to each divorcing partner.

5/ A certificate of registration of death shall be given to the person entitled to receive it in accordance with this Proclamation.

6/ A certificate of civil registration of adoption shall be given to the person who has declared the adoption in accordance with this Proclamation.

https://ethiodata.et/

**፵፱. ስለ ምስክር ወረቀት ክፍያ**

፩/ የሲቪል ምዝገባው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ መሰረት በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ላስመዘገበ ሰው ከክፍያ ነጻ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ መሰረት በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሲቪል ምዝገባውን ያላስመዘገበ ሰው የሲቪል ምዝገባ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው በዚህ አዋጅ መሰረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የተወሰነው የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም ነው፡፡

**፶. የማስረጃነት ክብደት**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፰ መሠረት የተሰጠ የምዝገባ ምስክር ወረቀት በክብር መዝገቡ ላይ ከሰፈሩት መረጃዎች ጋር እኩል የማስረጃነት ክብደት ይኖረዋል፡፡

**ክፍል አምስት**

**የክብር መዝገብ መረጃዎችን ስለማረም**

**፶፩. የአጻጻፍ ስህተትን ስለማረም**

፩/ የሲቪል ምዝገባ ያከናወነ የክብር መዝገብ ሹም ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው ጥያቄ መሠረት መሰረታዊ የትርጉም ለውጥ የማያመጡ የክብር መዝገብ መረጃዎችን የሚመለከት የአፃፃፍ ስህተትን ያርማል። ዝርዝር አፈፃፀሙ አገልግሎቱ በሚያወጣው በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ እርማቱ መሰረዝን የሚያስከትል ከሆነ መረጃው በሚነበብበት ሁኔታ ይሰረዛል፡፡

**49. Payment for Certificate**

1/ A person that performs civil registration within the time limit stated in Article 18 of this Proclamation shall be issued a certificate free of charge.

2/ Notwithstanding the provision under Sub-Articles (1) of this Article, if civil registration has not been completed within the prescribed time limit, under Article 18 of this Proclamation, a certificate of civil registration shall be issued upon payment of the service fee determined by the regulation issued by the Council of Ministers.

**50. Probative Value**

The certificate of registration issued in accordance with Article 48 of this Proclamation shall have equal probative value as the records of the register of civil status.

**SECTION FIVE**

**CORRECTION OF RECORDS OF REGISTER OF CIVIL STATUS**

**51. Correction of Clerical Mistakes**

1/ The officer of civil status shall, at the request of an interested party, make corrections that do not cause fundamental meaning change in the particulars of a register of civil status; detail implementation shall be determined by the Directive to be issued by the Service.

2/ Where the correction involves the cancellation of a word or number, the cancellation shall be carried out in a manner that the word or number remains legible.

https://ethiodata.et/

፫/ እርማቱ የምዝገባ ቅጹ ቅጅዎችንም የሚመለከት ሲሆን የክብር መዝገብ ሹሙ ስለእርማቱ ቀደም ሲል ቅጅዎቹ ለደረሳቸው አካላት ሁሉ ማሳወቅ አለበት፡፡

3/ Where the correction affects all copies of the registration form, the officer of civil status shall give notice of the same to all bodies which have already received such copies.

## ፶፪. ሌሎች እርማቶች

በፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ተመሥርቶ ካልሆነ በስተቀር ከአጻጻፍ ስህተት ውጭ የሆኑ በክብር መዝገብ ውስጥ የሰፈሩ መረጃዎችን የሚመለከቱ ሌሎች እርማቶችን ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## 52. Other Corrections

Corrections in particulars registered in a register of civil status, other than those involving clerical mistakes, may not be corrected except by virtue of a judgment given by a court.

## ፶፫. የእርምት ጥያቄ ስለማቅረብ

በክብር መዝገብ የሰፈረ መረጃ እንዲታረም በዐቃቢ ሕግ፣ በክብር መዝገብ ሹም ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ማንኛውም ሰው ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ሊቀርብ ይችላል፡፡

## 53. Application for Correction

An application for the correction of particulars registered in a register of civil status may be made to a court by the public prosecutor, officer of civil status, or any interested person.

## ፶፬. የፍርድ ቤት ውሳኔ

፩/ ፍርድ ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፫ መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ የቀድሞው ምዝገባ እንዲታረም ወይም አዲስ ምዝገባ እንዲከናወን ሊወስን ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፭ ወይም አንቀጽ ፶፮ መሠረት እርማት እስከሚደረግ ወይም አዲስ ምዝገባ እስከሚከናወን ድረስ ውሳኔው ከክብር መዝገቡ ጋር እኩል ክብደት ያለው ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል።

## 54. Decision of the Court

1/ The court may, upon examining the application submitted to it in accordance with Article 53 of this Proclamation, decide on the correction of the previous record or the drawing up of a new record.

2/ A judgment rendered pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall have equal probative value as the register of civil status until the record is corrected or a new record is drawn up in accordance with Article 55 or Article 56 of this Proclamation.

## ፶፭. የእርማት አመዘጋገብ

፩/ በመዝገቡ ውስጥ እንዲታረሙ የፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠባቸው መረጃዎች እንዲነበቡ ሆነው ይሰረዛሉ፡፡

## 55. Manner of Corrections

1/ The particulars of correction which is decided by the court shall be cancelled in the register of civil status in a manner that makes them remain legible.

https://ethiodata.et/

፪/ በተሰረዙት ምትክ አዲስ የሚገቡ ወይም ተጨማሪ ሆነው የሚገቡ መረጃዎች የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመጥቀስ በምዝገባ ቅጹ ጀርባ እንዲሰፍሩ ይደረጋል፡፡

፫/ የክብር መዝገብ ሹሙ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመጥቀስ የምዝገባ ቅጹ ቅጂዎች ቀደም ሲል የደረሳቸው አካላት ሁሉ እርማቱን እንዲያውቁት ማድረግ አለበት፡፡

**፶፮. <u>አዲስ ምዝገባ ስለማከናወን</u>**

፩/ በምዝገባው ላይ የሚደረገው እርማት ሰፊ ማስተካከያዎችን የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ ምዝገባው ተሰርዞ በአዲስ ምዝገባ እንዲተካ ሊያዝ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አዲስ ምዝገባ ሲከናወን፡-

ሀ) የቀድሞው የምዝገባ ቅጽ ተሰርዞ በጀርባው ላይ የፍርድ ቤቱን ውሳኔና አዲሱን ምዝገባ የያዘውን ቅጽ የሚያመለክት ማጣቀሻ ይሰፍራል፤

ለ) አዲሱን ምዝገባ በያዘው ቅጽ ጀርባ ላይ የፍርድ ቤቱን ውሳኔና የቀድሞውን ምዝገባ የያዘውን ቅጽ የሚያመለክት ማጣቀሻ ይሰፍራል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት አዲስ ምዝገባ ሲከናወን፡-

ሀ) የምዝገባ ቅጹ ቅጂዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፮ መሠረት ለሚመለከታቸው አካላት መላክ አለባቸው፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፰ መሠረት ጉዳዩ ለሚመለከተው ሰው ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

2/ The replaced particulars or the new ones added in the register shall be entered on the back of the registration form, with a reference to the judgment of the court.

3/ The officer of civil status shall, with reference to the judgment of the court, give notice of the corrections to all organs that have already received copies of the registration form.

**56. <u>Drawing up a New Record</u>**

1/ Where the correction of a record entails substantial changes, the court may order the annulment of the record and the drawing up of a new record in its place.

2/ Where a correction is made pursuant to Sub-Article (1) of this Article:

a) the previous registration form shall be cancelled and a reference to the judgment of the court and the new record shall be made on its backside;

b) a reference to the judgment of the court and the previous record shall be made on the back side of the new registration form.

3/ Where a new record is drawn up pursuant to this Article:

a) copies of the registration form shall be sent to the relevant organs in accordance with Article 46 of this Proclamation;

b) replacement certificate of registration shall be issued to the interested person in accordance with Article 48 of this Proclamation.

https://ethiodata.et/

፬/ የቀድሞ ምዝገባ እንዲታረም ወይም አዲስ ምዝገባ እንዲከናወን በፍርድ ቤት ከተወሰነ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀን ውስጥ እርማቱ ወይም ምዝገባው በውሳኔው መሰረት መከናወን አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## ስለ ቤተሰብ ምዝገባ

**፶፯. ቤተሰብ የማስመዝገብ ግዴታ**

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እና በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት የሚኖር የውጭ ሀገር ዜጋ የሚያስተዳድረውን ቤተሰብ በቤተሰብ መዝገብ ወይም በአገልግሎቱ በተዘጋጀው የቴክኖሎጂ መተግበሪያ ስርዓት ላይ ማስመዝገብ አለበት፡፡

**፶፰. ስለ ቤተሰብ ምዝገባ መዝጋቢ አካል**

አገልግሎቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የቤተሰብ ምዝገባ ተግባራትን ያከናውናል፣ ይመራል፣ የምዝገባ መረጃዎችን ያስተዳድራል፣ በብሔራዊ ደረጃ በመረጃ ቋት አደራጅቶ ይይዛል፡፡

**፶፱. የቤተሰብ ምዝገባ ይዘት**

የቤተሰብ ምዝገባ ሲከናወን የሚከተሉት መረጃዎች መመዝገብ አለባቸዉ፡-

፩/ ሙሉ ስም ከነአያት፣

፪/ ተመዝጋቢው የቀየረው ቀድሞ ሲጠራበት የነበረ የስም ስያሜ ካለ፣

፫/ የትውልድ ቀን፣ ወርና ዓ.ም፣

፬/ የትውልድ ቦታ፣

፭/ መደበኛ መኖሪያ ቦታ፣

፮/ ፆታ፣

፯/ የጋብቻ ሁኔታ፣

፰/ የሥራ ሁኔታ፣

፱/ ዜግነት፣

፲/ የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ልዩ ቁጥር እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች፣

፲፩/ ከተመዝጋቢው ጋር ያለው የቤተሰብ ግንኙነት

4/ When a court passes judgment for the correction or the annulment of the record and the drawing up of a new record in its place, the correction or the new registration shall be done according to the court judgment within 30 days of the passing of the court judgment.

## CHAPTER THREE
## FAMILY REGISTRATION

**57. Obligation to Family Registration**

Every Ethiopian citizen and a Foreign Citizen living permanently in Ethiopia shall declare his/her family member in the family registration form or on the digital applications prepared by the Service.

**58. Family Registration Organ**

The service shall register, coordinate, and administer the family registration data and archive it in the national data server.

**59. Contents of Family Registration**

The family registration form shall contain the following contents:

1/ Full name;

2/ Former name if any;

3/ Birth date;

4/ Place of birth;

5/ Place of residence;

6/ Sex;

7/ Marriage status;

8/ Occupation;

9/ Nationality;

10/ Digetal ID Unique Number;

11/ Family relationship and other related information;

https://ethiodata.et/

፲፪/ የሚኒስትሮች ም/ቤት በሚያወጣው ደንብ አገልግሎቱ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ሊጨምር ይችላል።

**፷. የመረጃዎች አመዘጋገብ**

፩/ ማንኛውም የቤተሰብ ምዝገባ የሚመዘገበው ለዚህ ተግባር በተዘጋጀው የምዝገባ ቅጽ ላይ ይሆናል፡፡

፪/ በምዝገባ ቅጹ የሚሰፍሩ የቤተሰብ ምዝገባ መረጃዎች በቴክኖሎጂ በተዘጋጀው መተግበሪያ ሥርዓት ላይ መመዝገብ አለባቸው፡፡

**፷፩. የቤተሰብ ምዝገባ ጊዜ**

፩/ ማንኛውም ቤተሰብ የሚያስተዳድረውን ቤተሰብ ሊያዘገይ የሚያስችል በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ምዝገባው በአካባቢው ከተጀመረበት ወይም አዲስ ቤተሰብ ወደ ቤተሰቡ ከተቀላቀለበት ጊዜ ጀምሮ በ፺ ቀናት ውስጥ ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ የቤተሰብ ምዝገባ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተፈጸመ እንደሆነ አስመዝጋቢው የዘገየበትን ምክንያት በማስረጃ አስደግፎ ማስመዝገብ አለበት፡፡

**፷፪. ስለ ማሳወቅ**

ማንኛውም የቤተሰብ አስተዳዳሪ የሚያስተዳድረው ቤተሰብ ከእሱ አስተዳዳሪነት በሚለይበት ወይም በሚወጣበት ጊዜ ለመዝጋቢው አካል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

12/ The Service may include other necessary particulars as stipulated by the Regulation issued by the Council of Ministers.

**60. Data Registration**

1/ Every family registration shall be registered in the registration form prepared for this purpose.

2/ Family registration data entered in the registration form must be registered on the digital application system.

**61. Family Registration Period**

1/ Every family shall register his/her family member within 90 days from the time registration starts in the area or from the time a new family member joins the family, unless there is a sufficient reason for the delay.

2/ The family shall present the reason for the dalliance of the registration to the officer if it was not done on time as per Sub-Article (1) of this Article.

**62. Notification**

Every family head shall notify the civil registration officer when the family member leaves or separated from the family.

https://ethiodata.et/

**፷፫. <u>የአጻጻፍ ስህተትን ስለማረም</u>**

፩/ መዝጋቢው አካል ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው ጥያቄ መሠረት መሰረታዊ የትርጉም ለውጥ የማያመጡ መረጃዎችን የሚመለከት የአፃፃፍ ስህተትን ያርማል፤ ዝርዝር አፈፃፀም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ መዝጋቢው እርማቱን ለአገልግሎቱ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

**፷፬. <u>ሌሎች እርማቶች</u>**

በፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ተመሥርቶ ካልሆነ በስተቀር ከአጻጻፍ ስህተት ውጭ የሆኑ በቤተሰብ መዝገብ ላይ የሰፈሩ መረጃዎችን የሚመለከቱ ሌሎች እርማቶችን ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

**፷፭. <u>የእርምት ጥያቄ ስለማቅረብ</u>**

በቤተሰብ መዝገብ ላይ የሰፈረ መረጃ እንዲታረም በቤተሰብ አስተዳዳሪው ወይም አስመዝጋቢው ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ማንኛውም ሰው ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**፷፮. <u>የፍርድ ቤት ውሳኔ</u>**

፩/ ፍርድ ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፭ መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ የቀድሞው ምዝገባ እንዲታረም ወይም አዲስ ምዝገባ እንዲከናወን ሊወስን ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯ መሠረት እርማት እስከሚደረግ ወይም አዲስ ምዝገባ እስከሚከናወን ድረስ ውሳኔው ከቀድሞው መዝገብ መረጃ ጋር እኩል ክብደት ያለው ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል።

**63. <u>Correction of Clerical Mistakes</u>**

1/ The family registration officer shall correct the clerical mistakes at the request of the person concerned in the form that does not cause a fundamental change of meaning. The detailed implementation shall be determined by the Directive to be issued.

2/ The family registration officer shall immediately notify the correction to the Service.

**64. <u>Other Corrections</u>**

It is prohibited to make other corrections regarding the information of the family register, other than clerical mistakes, unless and otherwise, it is the court's decision.

**65. <u>Application for Correction</u>**

An application may be made to the court by the family head or by declarants or any person concerned with the matter to correct the information registered in the family register.

**66. <u>Decision of the Court</u>**

1/ The court may examine the application submitted in accordance with Article 65 of this Proclamation and decide that the previous registration should be corrected or a new registration should be carried out.

2/ A court decision issued in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall serve as evidence of equal weight to the information of the previous record until a correction is made or a new registration is made in accordance with Article 67 of this Proclamation.

https://ethiodata.et/

## ፷፯. የእርማት አመዘጋገብ

፩/ በመዝገቡ ውስጥ እንዲታረሙ የፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠባቸው መረጃዎች እንዲነበቡ ሆነው ይሰረዛሉ፡፡

፪/ በተሰረዙት ምትክ የሚገቡ ወይም ተጨማሪ ሆነው የሚገቡ መረጃዎች የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመጥቀስ በመዝገቡ ላይ እንዲሰፍሩ ይደረጋል፡፡

፫/ መዝጋቢው አካል የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመጥቀስ የታረመውን መረጃ ለአገልግሎቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፷፰. ለመረጃ ተደራሽነት

፩/ አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የግል መረጃ ጥበቃን በተመለከተ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ መሰረት የተሰበሰበን ግላዊ መረጃ ያለተመዝጋቢው፣ አስመዝጋቢው ወይም የሚመለከተዉ ግለሰብ ፈቃድ ለሌላ ሰው መግለጽ ወይም አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የሲቪል ምዝገባን ወይም የቤተሰብ ምዝገባን አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎች በሕግ ስልጣን ለተሰጠው ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት ለሚመለከተው አካል ሊገለጹ ወይም ተላልፈው ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት መረጃዎችን ያገኘው አካል መረጃዎቹን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት ወይም ለሌላ ተግባር መጠቀም የለበትም፡፡

## 67. Manner of Correction

1/ The information registered shall be deleted by line on it so that it can be readable.

2/ The information to be replaced in place or any additional information shall be registered by mentioning the decision of the court.

3/ The family registration officer shall notify the Service about the corrected information by citing the court's decision.

## CHAPTER FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 68. Accessibility of Information

1/ Subject to the provisions of other relevant laws regarding the protection of personal information, it is prohibited to disclose or hand over the personal information collected by this Proclamation to another person without the consent of the person registered or declarant or the concerned individual.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this article, information collected regarding civil registration or family registration may be disclosed or transferred to the relevant body authorized by law or by court order.

3/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (2) of this Article, information specific to an individual shall not be handed over to another body or use it for any other purpose.

https://ethiodata.et/

፬/ የግለሰብን መረጃ ለሌላ ሰው መስጠት የሕዝብን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል ሆኖ ሲገኝ መረጃው እንዲሰጥ ተመዝጋቢው፣ አስመዝጋቢው ወይም የሚመለከተው ግለሰብ ቢፈቅድም መረጃው ለማንኛውም ሌላ ሰው መሰጠት የለበትም፡፡

፭/ አገልግሎቱ የተመረጡና ለስታቲስቲካዊ አገልግሎት የሚውሉ መረጃዎችን ለኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት መላክ አለበት፡፡

፮/ በተመዝጋቢው ወይም አስመዝጋቢው ወይም በሚመለከተው ግለሰብ ፈቃድ ወይም ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት የግለሰብ መረጃ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

## ፷፱. ስለሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት መጥፋት ወይም መበላሸት

፩/ የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለ መጥፋቱ ለፖሊስ ሪፖርት ማድረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ሲያቀርብ፣ ወይም

ለ) የተበላሸውን የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ሲያቀርብ፣ እና

ሐ) አመልካቹ በደንብ የተወሰነውን ክፍያ ሲፈጽም፣ ምትክ የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

4/ Where disclosure of information specific to an individual is likely to prejudice public interest, such information may not be disclosed to any other person irrespective of the consent of the person registered or declarant or the concerned individual.

5/ The Service shall send selected statistical data to the Ethiopian Statistical Service.

6/ Person entitled to obtain information specific to an individual by virtue of the consent of the individual or the declarant or an order of the competent court shall be provided with the information upon payment of the service fee prescribed by Regulation issued based on this Proclamation.

## 69. Loss or Damage of Civil Registration Certificate or National Identity Card

1/ When any person whose civil registration certificate is lost or damaged:

a) Presents evidence from the police stating that his civil registration certificate is lost or damaged; or

b) Presents the damaged civil registration certificate together with his application; and

c) When the applicant pays the service fee prescribed by Regulation issued based on this Proclamation, shall be replaced and issued.

https://ethiodata.et/

፪/ በሥራ ላይ በነበሩ ሕጎች ወይም ልማዳዊ አሠራሮች መሠረት በተከናወነ ሲቪል ምዝገባ የተሰጠ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ሰው በዚህ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች ሲያሟላ ከቀድሞ የክብር መዝገብ ላይ አስፈላጊ መረጃዎችን በመውሰድ ምትክ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፫/ የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት ወድቆ ያገኘ ማንኛውም ሰው የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ወይም የምዝገባ ጽህፈት ቤት ማስረከብ አለበት፡፡

፬/ አገልግሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው መረጃ እንደደረሰው የጠፋው የሲቪል ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለሕገወጥ አገልግሎት እንዳይውል በማዕከላዊ መረጃ ቋት መጥፋቱን ወድያውኑ መመዝገብ አለበት፡፡

፸. **<u>የመረጃ አያያዝና ደኅንነት</u>**

፩/ የሲቪል ምዝገባን ወይም የቤተሰብ ምዝገባን አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎች ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ አኳኋን በሥርዓት ተደራጅተው መቀመጥ አለባቸው፡፡

፪/ መረጃዎቹ የተለያዩ የኤሌክትሮኒክ መንገዶችን በመጠቀም ከሚደርሱ የሳይበር ጥቃቶች፣ ከስርቆትና ከመሰል የወንጀል ጥፋቶች መጠበቅ አለባቸው፡፡

፫/ መረጃዎቹን የያዙ ሰነዶች ከተፈጥሮና ሰውሰራሽ አደጋ መጠበቅ አለባቸው፡፡

2/ When a civil registration certificate given under Legal Provisions and Customary Practices formerly in effect has been lost or damaged, a replacement certificate shall be given upon fulfilment of preconditions listed in Sub-Article (1) of this Article by taking the necessary information from the former register of civil status.

3/ Any person who finds a civil registration certificate shall hand them over to the registration office or to the nearest police station.

4/ Upon receiving the information provided under Paragraph (a) of Sub-Article (1) of this Article, the Service shall register the loss of the civil registration certificate in the central database to ensure that not to be used for illegal purposes.

**70. <u>Managing and Safeguarding of Data</u>**

1/ The data gathered in relation to civil registration shall be kept properly to make them easily accessible for use.

2/ The data shall be protected from cyber-attacks, theft, or other similar criminal offenses.

3/ The document containing the data shall be protected from natural or manmade damages.

https://ethiodata.et/

፬/ ሰነዶቹ ጽሑፎቻቸው እንዳይደበዝዙና ሌሎች ጉዳቶች እንዳይደርሱባቸው በቂ ብርሃንና አየር ባለበት ቦታ መቀመጥ አለባቸው፡፡

**፸፩. <u>ስለውዝፍ ምዝገባ</u>**

አገልግሎቱ በሥራ ላይ በነበሩ ሕጎች ወይም ልማዳዊ አሠራሮች መሠረት ሳይመዘገብ የቆየ ውዝፍ የሲቪል ምዝገባ እና የቤተሰብ ምዝገባ ምዝገባን ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

**፸፪. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>**

በሥራ ላይ በነበሩ ሕጎች ወይም ልማዳዊ አሠራሮች መሠረት የተከናወኑ የሲቪል ምዝገባዎችና የተሰጡ የምስክር ወረቀት ማስረጃዎች ይህን አዋጅ እስካልተቃረኑ ድረስ ጸንተው ይቆያሉ፡፡

**፸፫. <u>አገልገሎት ስለማግኘት</u>**

ከአገልግሎቱ የምስክር ወረቀት የወሰደ ማንኛውም ሰው የክብር መዝገብ ቅጽ ቅጂ ከሚገኝበት ማንኛውም የምዝገባ ጽህፈት ቤት አገልግሎት የማግኘት መብት አለው፡፡

**፸፬. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>**

፩/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና የብሄራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፷/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፫/ ብሔራዊ መታወቂያን ከሚመለከቱ አንቀፆች ውጪ በወሳኝ ኩነት ምዝገባና የብሄራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፷/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) መሰረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ይህን አዋጅ

4/ The documents shall be kept in a place where there is sufficient air and light to protect registered data from risks of fading and other damages.

**71. <u>Backlog Registration</u>**

The Service shall set a backlog clearance system to record civil and family registration not registered based on the existing Laws or Traditional Practices.

**72. <u>Transitory Provisions</u>**

Civil registration process and evidence provided on the basis of the existing Laws or Customary Practices shall remain valid as long as they are not contrary to relevant laws.

**73. <u>Access to services</u>**

Any person who has been issued a civil registration certificate or national identification card from the Service, has the right to access services from the registration office where a copy of the registration exists.

**74. <u>Repealed Laws</u>**

1/ Vital Events Registration and National ID Proclamation No. 760/2012 (as amended) is hereby repealed.

2/ Any Law or Customary Practice inconsistent with this Proclamation shall not be applicable with respect to matters provided for by this Proc

3/ Except the Articles related to National ID Regulations and Directives issued pursuant to the vital events registration and national identification Proclamation No. 760/2012 (as amended) shall remain

https://ethiodata.et/

እስካልተቃረኑና በሌላ እስኪተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

in force until they are formally replaced by new ones as long as they are not inconsistent with this Proclamation.

**፸፭. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ያወጣል።

፪/ አገልግሎቱ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ መመሪያ ያወጣል።

**75. Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers shall issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Service shall issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulation issued in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

**፸፮. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**76. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**አዲስ አበባ መጋቢት ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዘዳንት**

**Done at Addis Ababa, On this 18th day of March, 2025**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://ethiodata.et/